# የጉብኝት ቦታዎችን ገደብ የለሽ ፓስ (unlimited pass) በመጠቀም ይወቁ




ይሳፈሩ፣ ይውረዱ፣ እንደገና ይሳፈሩ

የሀገራችንን ዋና ከተማ የሚጎበኙ ከሆነ እና በርከት ያለ ቦታዎችን ለማየት እቅድ ካለዎት፣ ሜትሮ ፓስ (Metro pass)ን በመጠቀም ጊዜና እና ገንዘብ ማዳን ይችላሉ።

በ1-፣ 3- እና 7- ቀን ገደብ የለሽ ፓስ (Unlimited Passes) በማንኛውም የሜትሮ ጣቢያ በሚያገኟቸው፣ የሜትሮ ባቡርን እና የሜትሮ አውቶቡስን፣ በማንኛውም ጊዜ ልብዎ እንደፈቀደ -እዚህ፣ እዚያ፣ በማንኛውም ቦታ መቆም የሚያገኙበት እድል ይሰጥዎታል።

መረጃ ሊቀየር ይችላል። 50-124 7-19

# ለሜትሮ የእርስዎ መመሪያ




# የአገልግሎት መስጫ ሰዓቶች

| | |
|---|---|
| ከሰኞ – ሐሙስ: | 5 a.m. - 11:30 p.m. |
| አርብ: | 5 a.m. - 1 a.m. |
| ቅዳሜ: | 7 a.m. - 1 a.m. |
| እሁድ: | 8 a.m. - 11 p.m. |

የመጨረሻው ባቡሩ የሚለቅበትን ጊዜያት፣ በጣቢያው አስተዳዳሪ ኪዮስክ ውስጥ ያግኙ። የሜትሮ አውቶቡስ የጊዜ ሰሌዳ እና የመመላለሻ ድግግሞች እንደየመስመሩ ሁኔታ ይለያያል። ለእርስዎ የሚሰራውን የጊዜ ሰሌዳ በwmata.com/schedules ያውጡ።

# የክፍያ ዋጋን መክፈል

## የሜትሮባቡር



የዋጋ ክፍያዎች፣ በጉዞው ርዝመት እና የተሳፈሩበት ጊዜ የሚለያይ እና በልዩ ዝግጅቶች ወቅትም የመለወጥ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። የSmarTrip® ካርድን፣ ከሜትሮ ጣቢያዎች ከሚገኘው የዋጋካርድ ማሽን ወይም ከwmata.com ይግዙ። ማንኛውም እድሜው አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ ደንበኛ፣ በሜትሮባብር መንቀሳቀሻ መስመሮች ውስጥ ለመግባት እና ለመውጣት የSmarTrip® ካርድን ሊኖረው ይገባል።

## የሜትሮአውቶቡስ



የክፍያ ዋጋ መጠኑ፣ በክፍያ መክተቻ ሳጥኖቹ ላይ ተለጥፏል። የSmarTrip® ካርድ ወይም ቶከን (token) ካልሆነ በስተቀር፣ ክፍያውን ለማድረግ የሚጠበቅብዎትን ክፍያ ትክክለኛውን ሂሳብ የምንዛሪ መጠን መክፈል አለብዎት። የሜትሮ አውቶቡስ አሽከርካሪዎች፣ ምንዛሪ የማይሰጡ እና ጥሬ ገንዘብም አይዙም።

# ልዩ የዋጋ ትመና፣ ለአረጋውያን እና ጉዳተኛ ዜጎች

አረጋውያን እና ጉዳተኛ ዜጎች፣ የአረጋውያን SmarTrip® ካርድ ወይም ቅናሽ ዋጋ ያለው SmarTrip® መታወቂያ በሚጠቀሙ ጊዜ የዋጋውን ግማሽ ብቻ ይከፍላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ wmata.com ይጎብኙ።

# ገንዘብ-ቆጣቢ ፓሶች (PASSES)

ሜትሮ ለሕይወትዎ ተስማሚ የሆነ፣ የቀን፣ የሳምንት እና የወር ገደብ የለሽ ፓስ (unlimited passes) በስፋት ምርጫዎችን  ይሰጣል። ከማንኛውም ጣቢያ ወይም በwmata.com.አንዱን መርጠው ይግዙ።

| ፓስ | | ዋጋ |
|---|---|---|
| ወሃዊ ፓስ* | ገደብ የለሽ | From $81.00 |
| የ7-ቀን ፓስ | ገደብ የለሽ | $58.00 |
| የ7-ቀን ፓስ | አጭር ጉዞ | $38.00 |
| የ3-ቀን ፓስ | ገደብ የለሽ | $28.00 |
| የ7-ቀን ፓስ | ክልላዊ አውቶቡስ | $15.00 |
| የ1-ቀን ፓስ | ገደብ የለሽ | $13.00 |

*በwmata.com  ላይ ብቻ የሚገኝ

**ክፍያዎችን እና ፓሶችን (PASSES) የት ይገዛሉ**

የSmarTrip® ካርዶችን እና ፓሶችን (passes) በwmata.com፤ በማንኛውም የሜትሮ ባቡር ጣቢያና በርካታ የመሸጫ ቦታዎች፡ wmata.com/stores ይግዙ።

# የሜትሮ ጣቢያዎችን መፈለግ




ረጅም ቡናማ ቀለም ያለው ቋሚ ላይ በትልቁ ‘M’ ያለበት የጣቢያ መግቢያ መሆኑን ያመላክታል። በዚሁ ቋሚ ላይ ወደጎን የተሰመረ ቀለም ደግሞ፣ በዚያ ጣቢያ የሚያልፉ መስመሮችን ያሳያል።

# በሜትሮ ጣቢያዎች መኪና ማቆም



የመኪና ማቆሚያዎች ለተሳፋሪዎች እና ለማይሳፈሩ የተለያየ ተመን አላቸው። ዝቅተኛውን የመኪና ማቆሚያ ተመን ለማግኘት፣ የማቆሚያ ሂሳቡን በዚያው በሁለት ሰዓት ውስጥ የሜትሮ ባቡር በተጠቀሙበት በSmarTrip® ካርድዎ ይክፈሉ።

# የሜትሮባቡር መገኛ



የአሳንሰር እና ተንቀሳቃስ ደረጃዎቹ የጣቢያውን መግቢያ ከባቡር መቆሚያ መድረኮቹ ጋር ያገናኛሉ። አሳንሰሩ ከተባላሸ፣ ተመላላሽ (shuttle) አውቶቡስ አገልግሎቶች ጠያቂ በሚኖር ጊዜ ይዘጋጃሉ።

የትኛዎቹ አሳንሰሮች እንደማይሰሩ ለማወቅ wmata.comን ይጎብኙ፣ በ202-962-1212 ይደውሉ፣ በጣቢያ አስተዳዳሪ ኪዮስክ ላይ ያለውን ሞኒተር ይመልከቱ ወይም በጣቢያው መቆሚያ መድረክ አመላካች የኤሌክትሪክ ምልክቶችን ይመልከቱ።

# መዘዋወሪያዎች

ሜትሮ (እና ሁሉም በአካባቢው የሚገኙ የአውቶቡስ መገናኛ ዘዴዎች) ከአውቶቡስ-ወደ-ባቡር ወይም ከባቡር-ወደ-አውቶቡስ በመዘዋወር ጊዜ፣ በሁለተኛው ጉዞ ላይ የ$0.50 ቅናሽ ያደርጋሉ። ከአውቶቡስ-ወደ-አውቶቡስ የሚደረግ ዝውውር ላይ፣ የሁለተኛው የአውቶቡስ ጉዞ ዋጋ ከመጀመሪያው እስከአልበጠ ድረስ ነፃ ነው። ከበለጠ ግን፣ ልዩነቱን መክፈል ይገባዎታል።

ቅናሽ ወይም ነፃ መዘዋወሪያን ለማግኘት፣ የጉዞ ክፍያውን በSmarTrip® ካርድ መክፍል ያስፈልጋል። በጥሬ ገንዘብ ወይም በፓስ (pass) ከከፈሉ፣ ቅናሹን ወይም ነፃ መዘዋወሪያውን አያገኙም። የመዘዋወሪያ የጊዜ ገደብ፣ ጉዞው ከተጀመረበት፣ መነሻ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው ጉዞ መጀመሪያ ድረስ ባለው ሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ነው።

# በጣቢያዎች ውስጥ WI-FI መጠቀም

አብዛኛዎቹ የሜትሮባቡር ጣቢያዎች ነፃ የwi-fi አገልግሎት ይሰጣሉ። “Metro-Public” የሚለውን መምረጥ፤ ከዚያም፣ደንብና መመሪያው መስማማትዎን ማመልከት።

# ደህንነት እና ጥበቃ

አስጊ ነገር ካዩ፣ ወደሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ መምሪያ በ696873 ቴክስት ያድርጉ።
በአደጋ ጊዜ፣ 911 ወይም 202-962-2121 ይደውሉ።

# ብስክሌት እና ሜትሮ

አብዛኛዎቹ የሜትሮ ጣቢያዎች የብስክሌት ማስቀመጫ ሲኖራቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚከራይ መቆለፊያ ቦታዎች ስላሏቸው፣ ወደ ጣቢያው ብስክሌትዎን ነድተው ከሄዱ በኋላ፣ በዚያ አቁመው፣ የሜትሮ ባቡር ወይም የሜትሮ አውቶቡስን መውሰድ ይችላሉ።

# በሜትሮባቡር ላይ

ብስክሌቶች በሜትሮ ባቡር ላይ ምንግዜም የተፈቀዱ ናቸው። ሆኖም ግን፣ ለሁሉም ደህንነት ሲባል፣ ብስክሌትዎን በጣም ሰው በበዛበት ባቡር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው። ሜትሮ፣ ልዩ ዝግጅቶች ወይም የሰው መብዛት ይከሰታል ተብሎ በሚገመትባቸው በሌላ ቀናት፤ ብስክሌቶችን የመከልከል መብቱ የተጠበቀ ነው።

# በሜትሮአውቶቡስ ላይ

ሁሉም የሜትሮ አውቶቡሶች፣ ሁለት ብስክሌቶችን የሚይዝ መጫኛ አላቸው።

መጫን፣ በደንብ ማሰር እና ብስክሌትዎን ከመጫኛው ላይ ማውረድ፣ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

ብስክሌትዎን ለመጫን ከአውቶቡሱ ፊት ለፊት ከመምጣትዎ በፊት፣ አውቶቡሱ እንደቆመ እና የአውቶቡስ ሹፌሩ እንዳየዎት እርግጠኛ ይሁኑ።

## POINTS OF INTEREST

| Point of interest | Station |
|---|---|
| African Art Museum | Smithsonian |
| Air and Space Museum | L'Enfant Plaza |
| American Art Museum | Gallery Place |
| American History Museum | Smithsonian |
| Audi Field | Navy Yard-Ballpark |
| Botanic Gardens | Federal Center SW |
| Bureau of Engraving & Printing | Smithsonian |
| Capital One Arena | Gallery Place |
| Capitol Building | Capitol South |
| Chinatown | Gallery Place |
| Constitution Hall | Farragut West |
| Convention Center | Mt Vernon Sq |
| Corcoran Gallery | Farragut West |
| D.C. Armory | Stadium-Armory |
| Entertainment & Sports Arena | Congress Heights |
| FedEx Field | Morgan Boulevard |
| Federal Bureau of Investigation | Metro Center |
| Folger Shakespeare Library | Capitol South |
| Freer Gallery | Smithsonian |
| Hirshhorn Museum | L'Enfant Plaza |
| Holocaust Museum | Smithsonian |
| Iwo Jima Memorial | Rosslyn |
| Jefferson Memorial | Smithsonian |
| Library of Congress | Capitol South |
| Lincoln Memorial | Foggy Bottom-GWU |
| Lisner Auditorium | Foggy Bottom-GWU |
| Martin Luther King Jr. Mem'l | Smithsonian |
| Masonic Temple | King Street-Old Town |
| Nat'l Academy of Sciences | Foggy Bottom-GWU |
| National Archives | Archives |
| National Building Museum | Judiciary Sq |
| National Gallery of Art | Archives |
| National Geographic Society | Farragut North |
| National Institutes of Health | Medical Center |
| National Law Enforcement Museum | Judiciary Sq |
| National Museum of African American History and Culture | Smithsonian |
| National Museum of the American Indian | L'Enfant Plaza |
| National Portrait Gallery | Gallery Place |
| National Postal Museum | Union Station |
| National Shrine of the Immaculate Conception | Brookland-CUA |
| National WWII Memorial | Smithsonian |
| National Zoo | Woodley Park |
| Nationals Ballpark | Navy Yard-Ballpark |
| Natural History Museum | Smithsonian |
| Phillips Collection | Dupont Circle |
| Renwick Gallery | Farragut West |
| RFK Stadium | Stadium-Armory |
| Sackler Gallery | Smithsonian |
| Smithsonian Castle | Smithsonian |
| Spy Museum | L'Enfant Plaza |
| State Department | Foggy Bottom-GWU |
| Supreme Court | Capitol South |
| Vietnam Veterans Memorials | Foggy Bottom-GWU |
| Washington Monument | Smithsonian |
| White House and Visitor Center | Federal Triangle |




# ተጨማሪ መረጃ በWMATA.COM

ጉዞዎን ያቅዱ፣ የአገልግሎት ሁኔታዎች እና ማስጠንቀቂያዎችን ያስተውሉ፣ የአውቶቡስ እና ባቡር መድረሻ ሰዓትን ወይም የጊዜ ሰሌዳዎችን ይመልከቱ፣ ስለሜትሮ አክሰስ (MetroAccess) (በግል የሚሰጥ የመጓጓዣ አገልግሎት)ን ይወቁ፣ የመሸጫ/የተጓጓዦች መሸጫ ቦታዎችን እና ሌሎችንም ይወቁ።

202-637-7000 TTY: 202-962-2033

facebook.com/metroforward

@MetroForward

@WMATA